# የኦነግ የፖለቲካ ቅሌት ወይስ የህወሃት/ኢሕአዴግ ዱክትርና?

(በኦነግ "ስም" በተበተነው ጽሁፍና በAFD ሰነዶች ዙሪያ ኮስታራ አመለካከቶች)

(ዘውዱ በቀለ)

ወደ ጽሁፌ ዋነኛ ዓላማ ከመግባቴ በፊት በጽሁፉ ለሚተረከው ጉዳይ ማገናዘቢያ እንዲሆነኝ ባስከፊነታቸው በታወቁት ሁለት የዓለም ጦርነቶች (የመጀመሪያውና ሁለተኛው) ወቅት አሜሪካንን ወደጦርነቱ ለማስገባት እንግሊዝ ተጫወተች ተብሎ የሚነገርላትን የሰነድ ማጥቆር ክስ ባጭሩ እንመልከት። ታሪክን ላነበበ እንደሚታወቀው ሁሉ አሜሪካ በሁለቱም ጦርነቶች ወቅት ከAllies ጎን በመቆም ወደ ጦርነቱ የገባችው ጦርነቶቹ ከተጀመሩና ብዙ ዕልቂት ከደረሰ በሁዋላ (በ1917 ና 1941) ነው።

አሜሪካንን ወደ ጦርነቱ ለማስገባት እንግሊዝ ተጫወተች ተብሎ የሚነገርላት ሚና በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት "ሉሲቴንያ" የተባለችውን የአሜሪካ ንግድ መርከብ ከብዙ መቶ ሲቪል ሠራተኞች ጋር በጀርመን ዩ-ቦት (U-boat) ተመትታ እንድትሰጥም ተደርጋለች የሚለውን ዜና በማስተላለፍና (አንዳንዶች መርከቧ የሰጠመችው በጠላት ጦር እንዳልሆነ ይናገራሉ) በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ደግሞ የናዚ መሪዎች ሜክሲኮን ከጀርመን ጎን አቁመው ወደ ጦርነቱ ለማስገባትና አሜሪካንን ለማጥቃት መስፈንጠሪያ ሆና እንድታገለግል የሚል የቴሌግራም መልዕክት ጠለፍን ብለውና ጽሁፉን "አክመውት" እንግሊዞች ለአሜሪካ ማስተላለፋቸውና አሜሪካንም በፐርል-ሀርበር አከታትሎ የደረሰባት የጃፓን ጥቃት ጥርጣሬዋን አጠናክሮላት ወደጦርነቱ እንደገባች ይነገራል። የእንግሊዝን የፖለቲካ ሤረኛነት ባህሪ ለሚያውቅ እንግሊዝን መጠርጠር ይኖርበታል፣ ግና አሜሪካም ሌላዋ እንግሊዝ ነበረች፣ አሁንም ነች።

ለግንዛቤ ያህል ደግሞ በወቅቱ አሜሪካ ትከተል ነበር ተብሎ የሚነገርላትንና ባመዛኙ ግን በደቡብ አሜሪካ ውስጥ በነበራት የጦረኛነትና የተስፋፊነት ባህሪ (Manifest Destiny) ባዶ ያደረገባትን "ራስን የማግለል" ፖሊሲ (Isolationist Policy)፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጋር በተያያዘ ከእንግሊዝና ከጀርመን በመረከብ የሠመረላትን የልዕለ-ሃያልነት "ማዕረግ" ከስሌታችን ውስጥ በማስገባት ለመመልከት እንሞክር።

*ወያኔና ኦነግ (ከላይ በተጠቀሰው ምሣሌ በቅደም-ተከተል እንግሊዝና አሜሪካ ብንላቸው)፣ በተለይም ደግሞ የቀድሞው፣ ይህንን የመሰለ ውስብስብ ዕንቆቅልሽ የመፍጠር ችሎታ የላቸውም ባይባልም በርዕሱ የተነሳውን ጥያቄ አያይዤ ከማነሳው ጽሁፍ ጋር ግን በዝርዝር ሳሳይ በምሥራቅ አፍሪቃ የልዕለ-ሃያልነት ቅዠት ያለውን አንዱን ወገን ብቻ ተጠያቂ ወደሚያደርግ አመለካከት የአንባቢዎቼን ትኩረት ለመሳብ እሞክራለሁ።*

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ ዋነኛ ምክንያት በአይጋ የወያኔ ወይም አፍቃሪ--ወያኔ ድረ-ገጽ (http://www.aigaforum.com) ላይ፣ ኦነግ ለአባላቱ አሠራጨው ተብሎ የወጣው ባለ 13-ገጽ የውይይት ጽሁፍ ነው። በጽሁፉ ዕቅፍ ውስጥ የተጠቃለሉ አደገኛ አመለካከቶች ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለኢትዮጵያዊነት ስሜት ከሚፈጥሩት

ከፍተኛ አደጋ አኳያ አንኳር መልዕክቱ ለሕዝብ ዳኝነት መጋለጥ አለበት የሚል ጽኑ ዕምነት ስላለኝ፤ በአደጋዎቹ ዋነኛ ባህሪያት ላይ በማተኮር ከጽሁፉ እያጣቀስኩ ለመተቸት እሞክራለሁ። ይህንን ከማድረጌ በፊት ግን ይህንን ጽሁፍ በተመለከተ በአንዳንድ ወገኖች የተሰጠውንና ከላይ በማገናዘቢያው እንዳመለከትኩት በወያኔ የመሠሪነት ባህሪ ላይ የተመረኮዘና ወያኔን ተጠርጣሪ የሚያደርግ ጤናማ ግምት አስመርኩዤ አንዳንድ ነጥቦችን ማለት እፈልጋለሁ። ግምቱ በግልጽ አማርኛ ሲነገር የሚከተለውን ይመስላል፦

*“በተቃዋሚ ሃይሎች በቅርቡ የተመሠረተውን ትብብር (ADF) ለማንኳሰስና ግቡንም እንዳይመታ ለማድረግ ጽሁፉ በወያኔ/ኢሕአዴግ ተዶክትሯል (TPLF/EPRDF-doctored document) የሚል አመለካከት አለ።”*

በርግጥም ከህወሀት/ኢሕአዴግ መሠሪ የፖለቲካ ባህሪ በመነሳት የዚህ ዓይነቱ የመከራከሪያ ይሁንታ (Probability) ከዕውነት የራቀ አይመስልም። ይሁንና የዚህን አመለካከት እርግጠኝነት ከተቻለ በማያዳግም መልኩ ለማረጋገጥ የጽሁፉን ባለቤት አንኳር መልዕክት (Thesis)፤ መንደርደሪያውንና መድረሻውን በአንክሮ መመርመር የግድ ይላል። ይህም ማለት ጽሁፉን ከሁለቱም ተጠርጣሪ ድርጅቶች ማለትም ከኦነግና ከወያኔ/ኢሕአዴግ ታሪካዊ አመጣጥ፤ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ከተጫወቱትና እየተጫወቱ ካሉት አደገኛ ሚናና አሁንም የመጀመሪያው (ኦነግ) ምናልባትም የመገንጠልን ጥያቄ ወደ ሥልጣን በመምጣት ለማመቻቸት፤ ሁለተኛው (ወያኔ) ደግሞ የያዘውን ሥልጣን ለማቆየት ከሚያደርጉት ግብግብና አንዳንዴም ተቀራርቦ ለመሥራት ከሚያሳዩት ፍላጎት (Diplomatic Rapprochement) አንጻር አቀናጅተን ለማየት እንሞክራለን።

ጽሁፉን ሁለት ሦስት ጊዜ ደጋግሜ ስላነበብኩት በእኔ ግምት በወያኔ የተፈበረከ ቅጥፈት (Hoax/Fraud) ነው ሊያሰኙና ላያሰኙ በሚችሉ ምክንያቶች ላይ፤ አቋሜን ላሁን ላዘግይና፤ በእሰጥ-አገባ መልኩ አንዳንድ አዳባሪ አመለካከቶችን ልሠንዝር፡

ሀ. <u>ህወሀት/ኢሕአዴግን ተጠርጣሪ ሊያደርጉት የሚያስችሉ ሦስት ምክንያቶች</u>

1) በትብብሩ (AFD) የመግባቢያ ማስታወሻና በደንቡ (Memorandum of Understanding and the Statue) በግልጽ እንደተቀመጠው ስብስቡ ከኢሕአዴግ “ለተጋጨው” ኤርትራ/ሻዕቢያ ታክቲካዊ ዕውቅና ከመስጠቱም ባሻገር እንደ አደራዳሪም የኤርትራ ተወካይ በስብሰባው መገኘቱ/ተገኝቷል መባሉ ለወያኔ አስደንጋጭ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። የዚህን ተቃራኒ አመለካከት፤ ማለትም ለምን የኤርትራ ጉዳይ ለአቶ መለስ ብዙም ራስ ምታት እንደማይሆን፤ በተራ ቁ. (ለ) ስር እመለስበታለሁና ዳኝነታችሁን ለጊዜውም ቢሆን አቆዩት፤

2) ህወሀት/ኢሕአዴግ ከኦነግ ጋር በርካታ ጦርነቶችን በማድረጉና ለብቀላ እንደሚጓዝ የማያሽልብ ጠላትና እንደ የጭቁን ብሔር መብት “አስጠባቂ” ተፎካካሪም ሊያየው ስለሚችል በሌሎች ድርጅቶች ጀርባ መግነኑን አይሻም፤ “ሁለት አውራ ዶሮ ባንድ ቤት አያድርምና”

3) በጊዜያዊነትም ቢሆን የሰብሰቡ መሳካት ያለኝን ወታደራዊ ድጋፍ ይሸረሽራል፤ የውጭ ድጋፌን ይቀንሳል፤ ሌሎችንም ሃይሎች (በተለይም ኢትዮጵያዊ ሃይሎችን) ያጠናክራል ከሚል የራሱ የህወሀት/ኢሕአዴግ ፍርሃት በመነሳት።

## ለ. <u>ህወሀት/ኢሕአዴግን እንዳይጠረጠር የሚያደርጉ አምስት ምክንያቶች</u>

1) የትብብሩን የመስማሚያ/መግባቢያ ማስታወሻ (Memorandum of Understanding) እና ሕጉን (Statue) በጥሞና ላነበበ የተደረገው ስምምነትም ሆነ AFDን በበላይነት የሚመራው ኦነግ (ከቀሪዎቹ የብሔር ድርጅቶች ጋር) የመገንጠል መብታቸውን የሚያስከብረውን የወያኔ ህገ-መንግሥት ተብዬ አይቃወሙትም ብቻ ሳይሆን ከልብና በስሜትም ይደግፉታል። ህወሐት/ኢሕአዴግምይህንን የሚቀበለው በደስታ ነው።

2) በትብብሩ ውስጥ የበላይነት ያላቸው እነዚሁ ወገኖች የግንቦት 97ቱን ሕዝባዊ ድልና ለዚህም የወደቁትን ሰማዕታት ጥያቄያቸው አድርገው አልወሰዱትም፤ ይህ ለወያኔ/ኢሕአዴግ ፈንጠዝያ ነው።

3) በአጀንዳቸውም ሆነ፤ ምናልባትም ገና ለሕዝብ ይፋ ባላደረጉት የመጨረሻው ስምምነታቸው፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ስላልተቀረጹ፤ ይህም ለወያኔ የወደፊት ህልውናም ሆነ ቀደም አድርጎ በኢትዮጵያ ህልውናና በልጆቿ ላይ ለፈጸማቸው በደሎች (የኤርትራን መገንጠል ጨምሮ) ቢያንስ ከእነዚህ ወገኖች በኩል ከሳሽ ስለማይኖረው። በተራ ቁ. (ሀ) እንደገለጽኩት የእነዚህ ወገኖች የሻዕቢያን/ኤርትራን ነጻነት ማወቅ የወያኔን ቻርተር መደገፍ ስለሆነ ወያኔን ብዙም አያሳስበውም። በአቶ መለስና በአቶ ኢሳይያስ መካከል ያለው በቆዳ ውፍረት የሚለካ ልዩነት ሲፈታ ግን የኢትዮጵያን ልዕልና ከማዳከም አንጻር ሲሸርቡ የኖሩበትና የቀጠሉበት ሴራ መልሶ ያገናኛቸዋል። አሁን ግን ባመዛኙ በትግራይ ህዝብ ግፊትም ይሁን በሌላ እንደጠላት ይተያያሉ፤ አንዱም ሌላውን ለማጥፋት የሚተኙ አይመስሉም። ያውራ ዶሮዎቹ ታሪክ መሆኑ ነው።

4) ይህ በኦነግ ተበተነ ወይም ወያኔ ፈበረከው የተባለው ጽሁፍና ከAFD አመሠራረት ጋር በተያያዘ፤ ምናልባትም በሻዕቢያ ድጋፍ፤ ከስብሰባ በፊት የተቀረጸው Memorandum of Understanding እና Statue ባመዛኙ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታ በመሆናቸውና የነዚህም ሰነዶች ደራሲ ወያኔ ባለመሆኑ፤ (ዝርዝሩን በሁዋላ እመለስበታለሁ) እና

5) በጽሁፉ ተደጋግሞ እንደተገለጸው የኦነግን የቆየ አቋም የሚያንጸባርቁ አባባሎች (<u>ለምሳሌ</u> - የትገሬና የአማራ የኢትዮጵያዊነት ስሜት፤ ነፍጠኝነት፤ በኦነግ ውስጥ ያለውን ልዩነት ለማስታረቅ ኦነግ የሚጠቀምበት የውስጥ ብቻ የሆነ ቋንቋ - ወዘተ) በወያኔ የጽሁፉ ደራሲነት ላይ የከረረ ጥያቄ ያስነሳሉ።

# ታዲያ የዚህ ጽሁፍ ባለቤት ማነው?

**ከዚህ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች ብዙ ናቸው። ጥቂቶቹንና ዋና ዋናዎቹን እናንሳ።**

1. በኦነግ ስም እስከተጻፈስ ድረስ ኦነግ ላለመሆኑ፤ የአቶ ዳውድ ኢብሳን "የአደጋ መከላከያ/መቀነሻ" የራዲዮ ማስተባበያ ወደጎን ትተን፤ ልናቀርብ የምንችለው ሌላ የመከራከሪያ ሃሳብ ምን ሊሆን ይችላል? ለምንስ አስፈለገ?
2. ኦነግ ከሆነስ የኦሮሚፋ ቋንቋ እያለ እንዴት በአማርኛ ተጻፈ?
3. እንዴትስ አድርጎ ከአባላቱ እጅ አፈተለከ? የሥርጎ-ገብ ሤራስ ይሆን?

እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በጽሁፌ መጨረሻ ላይ ለመመለስ እመክራለሁ። አሁን ግን በቅርቡ ከተቋቋመው ትብብር (AFD) ምሥረታ ጋር ተያይዞ፤ ምናልባትም ሁለት/ሦስት ወር አስቀድሞ፤ ኦነግ ለአባላቱ ለውይይት አስተላለፏል ብዬ እኔ የምጠረጥረውን ጽሁፍ አንድና ጽሁፍ ሁለት አጣምረን በገጽ እያጣቀስን እንነጋገር።

<u>ጥቅስ አንድ (ገጽ 1 ና ገጽ 7)፡</u> ግንባር/ስብስብ ለምን እንደሚያስፈልግና ስሙም ምን መባል እንደሚገባው ሲጽፍ።

**"ባስተማማኝ ደረጃ ላይ የደረሰው የኦሮሞ ነጻነት ትግል በተቻለ ፍጥነት ከግቡ እንዲደርስ ለማስቻል ትብብር (Alliance) መፍጠር ላይ ተስፋ በማድረግ የትግል አቅጣጫ መንደፍ አስፈልጓል (1) <u>ኦነግ</u> የዚህ ግንባር ስም ኢትዮጵያ የሚል በውስጡ የሌለው እንዲሆንና በAlliance (ግንባር) ስም ብቻ የሚጠራ ይሆናል የሚል አቋም አለው። ስሙም (Alliance for freedom and democracy) የሚል ይሆናል (ገጽ 7)" ይላል።**

<u>ግምገማ፡</u>

"ባስተማማኝ ደረጃ" የሚለው አባባል ምናልባትም ኦነግ በኤርትራ አደራዳሪነት ከሌሎች መሰል የብሔር ድርጅቶች ጋር ያደረጋቸውን ስምምነቶችና ከሌሎችም ተቃዋሚዎች ጋር ይደረጉ የነበሩ "አቅም-ገንቢ" መቀራረቦችን ሊያመላክት ይችላል። ከግቡ የሚደርሰው "የኦሮሞ የነጻነት ትግል" የሚለውም አባባል ይዘት ለአንባቢው ግልጽ ይመስለኛል-ነጻነት ማለት መገንጠል ነው፤ ሌላ ሊሆን አይችልም። የነጻነት ትርጉም አገባቦች፡ 1) ከቅኝ ገዥ/ወራሪ ነጻ መሆን፤
2) ከባርነት ነጻ መሆን ናቸው። ከሁለቱ የትኛውን ማለታቸው ይሆን? "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት" የሚለው አባባል በርግጥ የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው (ታሪካዊ መነሻውም ከቅኝ ግዛትና ከመስፋፋት (የጀርመን፤ የቱርክ፤ ወ.ዘ.ተ) ፖሊሲ ጋር ተያይዞ ባውሮጳ ውስጥ የነበረውን ችግር ለመፍታት በLeague of Nations የተጠነሰሰ ሃሳብ እንጂ፤ በአንድ አሃዳዊ አገር ውስጥ በተለያዩ ጎሣዎች መካከል ለሚኖረው ችግር መፍቻ ዘዴ እንዲሆን ታስቦ አልነበረም)። Alliance for Freedom and Democracy የሚለውና የሆላንዱ ስብስብ የተጠራበት ስምም አስቀድሞ መቀረጹን አንድ በሉልኝ፤ ይህም በተበተነው ጽሁፍ ውስጥ ተገልጿል። የUEDF

ተከታታይ መግለጫዎችም ሆኑ ለሕዝብ የተበተነው MOU እና Statue የሚያረጋግጡት ሰነዶቹ አስቀድመው ስለመቀረጻቸው ነው።

<u>ጥቅስ ሁለት (ገጽ 2)</u>፡ የኦነግን ራዕይና ስትራቴጂካዊ ግብ በተመለከተ

"1) የኦሮሞን ሕዝብ ለሥልጣን ማብቃት፤
2) ኦሮሞን በኦሮሚያ ላይ የባለ-ሀገርነቱን መብት (Sovereignty) ለማግኘት
የሚፈልገውን በማስያዝ የሚረጋገጥ ይሆናል፤ 3) በአግባቡ አስልተን
ከገባንበት ኦነግ ድል አድርጎ ኦሮሚያን የአፍሪቃ ቀንድ ሃያል ሀገር
ሊያደርግ ይችላል። (10)"

<u>ግምገማ</u>፡

በመሠረቱ በዚህ ጸሀፊ አመለካከት የኦሮሞን ህዝብም ሆነ የሌሎችን የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መሠረታዊ የሆኑና ከማስረጃ ጋር የተያያዙትንና የኢትዮጵያን ህልውና ጥያቄ ውስጥ የማያስገቡትን የመብትና የፍትህ ጥያቄዎች ወደፊት በኢትዮጵያ የሚመሠረተው ህጋዊ መንግሥት ባግባቡ ማስተናገድ እንዳለበት አጥብቆ ያምናል፤ ለዚህም የበኩሉን ሁሉ ትግል ያደርጋል። ከዚህ ውጭ ግን በጎሣ ላይ የተመሠረተና ሌላውን የሚያገልል ማናቸውንም መንግሥታዊ ሥርዓት አጥብቆ ይዋጋል። ይህንን ካልኩ በሁዋላ ወደ ጽሁፌ ዋነኛ ዓላማ ልመለስ።

ከላይ በጥቅሱ እንደተመለከተው "የኦሮሞን ሕዝብ ለሥልጣን ማብቃት"፤ "ኦሮሞን በኦሮሚያ ላይ የባለሃገርነቱን (ሉዓላዊነቱን?) መብት ማረጋገጥ" እና "ኦሮሚያን የአፍሪቃ ቀንድ ሃያል ሀገር ማድረግ" የሚሉትን ኮስተር ያሉና አደገኛ የሆኑ አመለካከቶች ስንገመግም፡

1) "ኦሮሞን ለሥልጣን ማብቃት" የሚለው ራስን በራስ ከማስተዳደር ፌደራላዊ መርህ አኳያ፤ በጎሣ ሳይሆን፤ በቀጠና (ሪጅን) ላይ ተመሥርቶ የሚቀርብ መከራከሪያ ከሆነ ብዙም ላያወዛግብ ይችላል። ሆኖም በዚህ አባባል ስር የተካተቱና ጥያቄ ሊያስነሱ የሚችሉ ሁለት ተጨማሪ ትርጓሜዎች ማለትም፡

   ሀ) የኦሮሞን ህዝብ መብት ለማስከበር ብቻ ኦነግን ወደ መንግሥት ሥልጣን ለብቻው አምጥቶ ይግዛ ማለት ከሆነ፤

   ለ) በኦነግ አመለካከት ኦሮሞ የሚላቸውን ወገኖቻችንን ሁሉ ከሆነለት በጎሠኝነት የDNA ጥናትና ምርምር *ከሌላው ጎሣ "አጽድቶ" አውጥቶና* ህዝቡ የሚሠፍርበትን መሬት አልሞ፤ ለክቶና ቆርጦ ከኢትዮጵያ ዕቅፍ በማውጣት በተ.መ.ድ የምትመዘገብ ሉዓላዊት የሆነችና ኦሮሚያ የምትባል አገር እንፍጠር ማለት ከሆነ የበርካታውን ህዝብ (ከ80 በላይ ልዩ ልዩ ጎሣዎች) መብት የሚጋፋ አደገኛ አመለካከት ይመስለኛል።

2) በጥቅሱ እንደተመለከተው ተከታትለው ከሚመጡት አመለካከቶችም መፍረድ ካስፈለገ በግልጽ አማርኛ "ኦሮሚያና ሉዓላዊነት፤ ኦሮሚያና የአፍሪቃ ቀንድ ሃያል አገርነት" በማያሻማ ሁኔታ ተቀምጠዋል።

3) ይህ ዓይነቱ አመለካከትም የኦነግ የቆየ ፖሊሲ መሆኑንና ይህንንም ፖሊሲ በማናቸውም ወቅት ሙሉ ለሙሉ አለማንሳቱን ማወቅ ይጠበቅብናል። ለአብነት ያህል ከታች የተመለከተውንና አሁንም ከADF ምሥረታ በሁዋላ እንኳ በኦነግ ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘውን የኦነግ ራዕይ (Mission) መመልከቱ ይጠቅማል።

**The Oromo Liberation Front (OLF) is a political organization established in 1973 by Oromo nationalists to lead the *national liberation* struggle of the Oromo people against *the Abyssinian colonial rule. (Emphasis mine)***
*http://www.oromoliberationfront.org/OLFMission.htm*

ከላይ በጥቅሱ ከተመለከተው በተጨማሪ በዚሁ ድረ-ገጽ ላይ ያለውን የኦነግ ዓላማዎች (Objectives) በዝርዝር ያንብቡ፤ ከዚያም ትዕግሥቱ ካለዎት በኦነግ የፖለቲካ ካርቶግራፊር አመለካከት ኦሮሚያ ምን እንደምትመስልና ምን እንደምታክል OromiaBriefs በሚለው ስር ይመልከቱ። በዚህም ከተራራ የከበደና የሂትለርን ቅዠት የመሰለ የኦነግ ህልም የወደፊቷ ኦሮሚያ ከኢትዮጵያ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ውስጥ ከሲሦ በላይ ያቀፈውን ካርታ ያገኛሉ። ህወሐት/ኢሕአዴግ አወጣ የተባለው ካርታ ከዚህ የገነነ ይሆን?

የኦነግ መሪዎች በየታሪካዊ አጋጣሚውና በትግሉ መስቀለኛ መንገድ መዳረሻዎች ሲደርሱና ግፊት ሲበዛባቸው ወይም አጋጣሚውን በመጠቀም ለአጀንዳ ማስፈንጠሪያነት በሚሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አንዳንድ ብዥታዎች ሊፈጥሩብን ይችሉ ይሆናል። ይህ ማለት ግን አንዳንድ ጥያቄዎቻቸው አልረገቡም ወይም ደግሞ በድርጅት ደረጃ የተሠራጩና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋ ባይሆን ኖሮ ወደዘር ማጥፋት አመለካከትና ድርጊት ሊገፉ ይችሉ የነበሩ ፖሊሲዎቻቸውና፡ በወያኔም የ"ኢንተር-ሃምዌ" መርዘኛ ቅጥፈት (Demagogy) ተደግፎ፤ ይነዙ የነበሩት ጭፍን ጥላቻዎቻቸው አልቀነሱም ማለት እንዳልሆነ ግን አንባቢ ባግባቡ እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ። ከዚህም ገፍቼ መሄድ እችላለሁ - ከተቃዋሚ ሃይሎች ጋር የሚያደርጉት መቀራረብ ሁሉ ባንድ አቅጣጫ ብቻ መተርጎም አለበት የሚልም ጠጣር ዕምነት የለኝም።

<u>ጥቅስ ሦስት (ገጽ 2፤ 3ና 10)፡</u> የኦነግን ራዕይ/ግብ እንዳይመታ ለማድረግ ሊያደናቅፉ የሚችሉ መሰናክሎች (በድርጅቱ አመለካከት)

"1) የወያኔ መንግሥት ጭካኔና ግድያ፤ 2) ኢትዮጵያ በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ ያላት ስምና ዝና (Myth)፤ <u>[3) ስምምነቱ (Alliance) ካልሠመረና ብቻችንን ወይም ደግሞ ከደቡብ የብሔር ድርጅቶች ጋር ብቻ እንጓዝ ካልን ደግሞ በኢትዮጵያ ስም የተደራጁት ሃይሎች *(ቅንጅትና ሕብረትን ማለታቸው ይመስለኛል)* ዕንቅፋት ይሆኑብናል፤ ሰሜን ሃይሎችን (አማራና ትግሬን) ያስታርቃል። እነዚህ ሁለቱ በሥልጣን ላይ ይጣሉ እንጂ ኢትዮጵያቸውን ለማኖር ያላቸው አቋም አንድ ነው።]"</u>

***ግምገማ፣***

*ከላይ ከተመለከቱት ጥቅሶች ውስጥ ቃል በቃል ያሠፈርኩት ተራ ቁ. 1 እና 2ን ብቻ ነው። ሁለቱም የተወሰዱት ከጽሁፉ የመጀመሪያው ክፍል ነው። በተራ ቁ. 3 የተመለከተውን ነጥብ በተመለከተ ግን ጸሐፊዎቹ በሆላንዱ ስብስብ ችግሩ ይፈታል በሚል የአስቀድሞ ብያኔ ላይ ስለደረሱ ይመስለኛል ባንድነት አጠቃለውና ጎላ አድርገው በመጀመሪያው ጽሁፍ ውስጥ አላቀረቡትም። ጉዳዩን እንደ ዕንቅፋት የተመለከቱትና በሁለተኛው ጽሁፍ ውስጥ ከግንባር መፍጠር ጋር በተያያዘ ጉዳይ ያቀረቡት፤ ምናልባትም በድርጅታቸው ውስጥ የተነሱትን ቅዋሜዎችና ጥርጣሬዎች ለማስወገድ የሰጧቸው ምላሾች ሳይሆኑ አይቀርም የሚል ዕምነት አለኝ። ስለዚህም ተራ ቁጥር 3-ን የቀረጽኩት መሠረታዊ መከራከሪያቸውን ሳልለውጥ በገጽ 10 ላይ ተበታትነው ያሉትን ሃሳቦች በማሰባሰብ ነው።*

*በኦነግ አመለካከት፤ ሌሎችም ተቃዋሚዎች የሚጋሩት ብቻ ሳይሆን አስቀድመው የቀረጹት ዕውነታ መሆኑ ነው፤ የወያኔ የጭካኔ አገዛዝና ግድያ እነሱ እንደሚሉት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ወገኖቻችን ላይ በገፍና በግፍ ተፈጽሟል፤ አሁንም ቀጥሏል። የጸጥታ ሃይሉም ጭፍን ታማኝነትና ህዝብን ለመጨፍጨፍ ያለው ፈቃደኝነት በተግባር የተገለጸ ስለሆነ በአባባሉ ዕውነተኝነት ላይ ጥያቄ አላነሳበትም። ከላይ በተራ ቁ. (2) እና (3) የተጠቀሱትን አመለካከቶች በቅጡ ስንገመግም ግን ወደ ኦነግ መሠረታዊ የሆኑና የቆዩ መከራከሪያዎች ይመልሰናል። ጠባብ ፍላጎታቸውን ከግቡ ከማድረስ አኳያ ሻዕቢያ (ከዚያም በፊት ጀብሃ) ፤ ህወሀትና ኦነግ ከቅኝ ገዢዎች (በተለይም ደግሞ ከፋሽስት ኢጣልያ አደገኛ ርዕዮተኞች* (Ideologues) *የወረሱትንና ለመገንጠልም ሆነ ለማስገንጠል የተከታዮቻቸውን አዕምሮ በመስለብ ሲጠቀሙባቸው ከነበሩት የቅጥፈት ስልቶቻቸው አንደኛውና ዋነኛው ኢትዮጵያን የአንድ "ገናና ብሔር/አማራ" ገነት/ነጻ መሬትና የሌሎች ብሔረሰቦች ገሃነም/እስር ቤት አድርጎና አጥቁሮ ማቅረብ ነበር። ኦነግ ይህንን ጥያቄ በተመለከተ አሁን ያለውን አቋም ገና ግልጽ አላደረገም። ከላይ በጥቅሱም እንደተመለከተው የቀድሞ አቋሙን የሚያጠናክር እንጂ የሚያላላ መልዕክት የለውም። የተለወጠ ነገር ቢኖር የዓለም መንግሥታት በኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ ዙሪያ በወቅቱ ሊኖራቸው ከሚችለው አቋም አንጻር (በኤርትራ ጉዳይ የነበራቸውን አቋም ስለምናውቅ ይህም የከረረ ጥያቄ የሚነሳበት ጉዳይ ነው) መፍረሷን አይፈልጉም የሚለው አባባል ነው። የኢትዮጵያንም የአንድነት፤ የጀግንነትና የጥቁር ሕዝብ አርዓያነት ዕውነተኛ ታሪክ እነርሱም እንደቅኝ ገዥዎቹ ሁሉ በፖለቲካ ሎሌነታቸው* Myth *ብለውታል። የዚህ ዓይነቱ ክህደት በተለያዩ ከላሽ የታሪክ ጸሀፊዎች* (Revisionist Historians) *በኢትዮጵያ ላይ የተነጣጠረ ሤራ ስለመደጋገሙና ምንጩም ምን ሊሆን እንደሚችል በቅርቡ ታትሞ የወጣውን የዶ/ር ዳንኤል ክንዴን መጽሐፍ በጥሞና ያንብቡ።*[1]

*በኦነግ የቅርብ ጊዜ አመለካከት ደግሞ የውጭ ሃይሎች የኢትዮጵያን መከፋፈል "ስለማይፈልጉ" ባጭር ጊዜ ውስጥ ኦሮሚያን የመፍጠር ይሁንታ ችግር ይገጥመዋል ማለት ነው። ስለዚህም በቅድሚያ "በእኔ አመራር ከኢትዮጵያ ሃይሎች*

---

[1] Kendie, D. (2005) The Five Dimensions of the Eritrean Conflict (1941-2004), USA: Signature Book Printing Inc.

ጋር በመሥራት ይህንን አመለካከት መለወጥና ለግንጠላውም አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር ይቻላል"፣ የሚል ዕምነት ኦነግ አለው ማለት ነው። ስለዚህም ይህንን ዓላማ ለማሳካት ኦነግ የትብብሩን አመራር ለማንም አሳልፎ መስጠት የለበትም። ከADF ምሥረታም ጋር ተያይዞ የተከሰተው ሃቅ ይህ መሆኑ ነው።

በጥቅሱ ተራ ቁ. (3) የተመለከተውንና የኦነግን የቆየና አሁንም ከድረ-ገጹ ያልወጣውን አደገኛ አቋም እንመልከት። እንግዲህ በኦነግ አመለካከት (ይህ ጽሁፍ የርሱ ከሆነ) ይህ ስብስብ የተፈለገው፦ ዓላማው እንዳይሳካ በግንባር ቀደምነት ዕንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉትንና በኢትዮጵያ ስም ከተደራጁት ሃይሎች ዋነኞቹን ማለትም ሕብረትና ቅንጅትን በቁጥጥሩ ስር "ለማስገባት" ነው። ከዚህም አልፎ እነዚህን ሃይሎች ትብብሩ ውስጥ በማስገባትና ያልጎላም የፖለቲካ ሚና በመስጠት፣

ሀ) ዕንቅፋት ቁጥር አንድን (ወያኔን/ኢሕአዴግን) አጥፍቶ ጥርጊያውን ማሳመር ይቻላል (ኦነግ ይህንን የራሱን ጥረት የሚያመሳስለው በስብስብ (Alliance of the Willing) የ"ጸረ-ሽብርተኝነትን" ጦርነት ከምታካሂደው ከአሜሪካ ጋር ነው)፣

ለ) ዕንቅፋት ቁጥር ሁለትና ሦስትን ደግሞ ከኢትዮጵያ የስትራቴጂክ ጥቅም አኳያ (የአንድነቷና ሉዓላዊነቷ ጥያቄ) ከሚመስላቸው ከትግራይ ሕዝብ ጋር ሊያብሩና የጸረ-ኦነግ ግንባር ሊፈጥሩ የሚችሉ የ"አማራ" የሚሏቸው ሃይሎች መሆናቸው ነው። ስለዚህም እነዚህን ሃይሎች ማዳከም/መዋጥ፣ (ከኢሕአዴግ አመሠራረትና ሂደት ትምህርት በመቅሰም ይመስላል)፣ ይቻላል ወይም ደግሞ የእኛ አቅም ከፍተኛ ስለሆነ እነሱንም ቢሆን በሂደት መደምሰስ አያቅተንም ማለቱ ነው።

| |
|---|
| ከዚህ በላይ ያቀረብኳቸው ጥቅሶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ጥቅሶቹ የስብስቡን የስምምነት ሰነዶች አንኳር ሃሳቦችና የሂደቱን ችግር የጀርባ አመጣጥ ሙሉ ለሙሉ ስለሚያሳዩ - የጽሁፉን ባለቤት ከወያኔ ይልቅ ኦነግ እንደሆነ በግልጽ ያስቀምጣሉ። |

## ማጠናከሪያ

ከዚህ ቀጥሎም በማጠናከሪያነት የADFን የስምምነት ሰነድ (Memorandum of Understanding) እና ደንቡን (Statue) ሁኔታው በፈጠረው ፈንጠዝያ ተገፍተው አመለካከታቸውን አዘናጊና ትጥቅ-አስፈች በሆነ መልኩ በነጻ ከነዙት በርካታ ጸሃፊዎች (ምሣሌ፡ አቶ (ዶ/ር?) ፈቃደ ሸዋቀናና አቶ ያሬድ ጥበቡ) አመለካከት ሳይሆን፣ በአትኩሮት ገምግመውና ጥርጣሬያቸውን ለሕዝብ ዳኝነት አውጥተው ካስቀመጡት ግለሰቦች (ለምሣሌ - አቶ ሰለሞን ገ/ስላሤ) ና ስብስቦች (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረት/ኢ.ዴ.ሃህ ሦስት መግለጫዎች [በተለይም "ራዕያችን - ስጋታችን" በሚል ርዕስ የወጣው ባለ 9 ገጽ ሦስተኛው መግለጫ] እና በቅርቡም በኢትዮጵያ የዴሞክራሲና ማሕበራዊ ፍትህ የጥናት ማዕከል (CDSJE) ተጽፎ የወጣ ጽሁፍ) ያቀረቧቸውን ግምገማዎች እየተጋራሁ የራሴን ግምገማ ደግሞ በ 7 (ሰባት) ነጥቦች ዙሪያ አቀርባለሁ። ሌሎችም መጠነኛ ልዩነት ቢኖረኝም ክብር የምሰጣቸውና ከፍትህ አኳያ የተጻፉ ጽሁፎች (ለምሣሌ - የአቶ ኦባንግ ኦ. ሜቶ Anuak Justice Council] እና ሌሎችም አሉ። በመጨረሻም በጽሁፌ መጀመሪያ አካባቢ ገጽ 4 ላይ ያነሳሁዋቸውንና እመለስባቸዋለሁ ያልኳቸውን ጥያቄዎች፣ ኦነግ በቅርቡ ካወጣው ማስተባበያ ጋር አያይዤ ለመመለስ በመሞከርና ለተቃዋሚ

ድርጅቶችም (ኦነግን ጨምሮ) አንዳንድ ጥያቄዎችን በመወርወር ጽሁፌን እደመድማለሁ።

<u>በስምምነቱ ሰነዶች ውስጥ የታቀፉ መሠረታዊ ችግሮችን በተመለከተ</u>

1. ከኢዴሃህ መግለጫዎችም ሆነ ከሌሎች ምንጮች እንደሰማነው፣ አጀንዳውም ሆነ ሁለቱ ሰነዶች (MOU & Statue) ስብሰባውን በጠራው ኦነግ (ምናልባትም የኤርትራና የሌላ ባዕድ ሃይል እጅ ታክሎበት) አስቀድመው ተወጥውጠው ስብሰባው አንድ ሰዓት ተኩል ሲቀረው ለስብሰባው ዕድምተኞች እንደተሰጡ ይነገራል። ይህ ክስም ትክክል ይመስላል ምክንያቱም ቢባል ስምምነቱን ያልፈረመውን የኢዴሃህንም ስም ጨምሮ አውጥቷል። "ወጡ ሳይወጠወጥ የወስከንባው ቁጢጥ" ወይስ ከዚህ የከፋና የከረፋ ሂደት? የሂደቱ ዴሞክራሲያዊነትና ፍትሃዊነትስ ከምኑ ላይ ነው?

2. <u>ሁለቱም ሰነዶች በስም አቀራረጽ (MOU፣ገጽ-1)</u>፡ የስብስቡ ዓላማ በርግጥ የኢትዮጵያን ችግሮች ለመፍታት ከሆነ እንዴት የኢትዮጵያ ስም ሳይኖርበት ቀረ? መሠረታዊ ጥያቄዎቻችንስ ሰላም ማምጣት፣ ማሕበራዊ ፍትህና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ሆነው ሳለ፣ ከቅኝ ግዛት ጋር የተየቃያዘ ጥያቄ ይመስል ነጻነት (Freedom) የሚለው ቃል ለምን ተደነቀረበት? የወያኔ ህገ-መንግሥት ተብዬ አንቀጽ 39ን እንደተሰባሪ ሸክላ ለመንከባከብ፣ ለመከላከል?

3. <u>የስብስቡን ዋነኛ ቋንቋ በተመለከተ (MOU ገጽ 2 እና Statue ገጽ 2)</u>፡ የዳበሩ፣ ኢትዮጵያን የሚያኮሩና ኢትዮጵያዊነትን የሚያደምቁ፣ ብሎም ብዙ ህዝብ የሚግባባቸው ያገር ቋንቋዎች (<u>ለምሣሌ</u>፡ ኦሮምኛ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ ወ.ዘ.ተ) እያሉ የባዕዱ ቋንቋ እንግሊዝኛ እንዲሆን ለምን ተመረጠ? የነጭ ግፌት አለ ማለት ነው?

4. <u>ከኤርትራ ጋር መልካም ግንኙነትና እህትማማችነትን መመሥረት (MOU ገጽ 3)</u>፡ የሚለው አባባል ኤርትራን እኛ በወያኔ ቻርተር አማካይነት በአገርነት እንደተቀበልናት ሁሉ እናንተም (ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች) ተቀበሏትና ለእኛም የወደፊት ዕቅድ የመስፈንጠሪያ መድረክ (Springboard) ወይም እንደነ TPDM እና OPDO ዓይነቶቹ የወያኔ መሰላሎች እናንተም ለእኔ መሰላል ሁኑኝ ማለት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

5. <u>የሚቀጥለውንና ሠፋ ያለውን (ምናልባትም ወያኔን የሚጨምረውን) ጉባዔ በተመለከተ (Statue: አንቀጽ 1፣ ንዑስ አንቀጽ 2)</u>፡ ይህንን በተመለከተ ያለኝ ችግር የሃይል ሚዛኑን ከለወጡ በሁዋላ ወያኔን አስገድዶ ተቀባይነት ወደሚኖረው የሽግግር መንግሥት ምሥረታ ስብሰባ ማምጣት የሚለው ይሁንታ ሳይሆን፣ የወያኔን ህገ-መንግሥት ተብዬ እንቀበለው/አንለውጠው የሚል ዓይነት አመለካከቱ ነው። "ሥጋውን ጠልቶ መረቁን" ይሏል ይህ ነው። መሠረታዊው የኢትዮጵያ ችግር የወያኔ ህገ-መንግሥት ይመስለኛል፣ ኦነግ ግን ይህንን እኔ ችግር የምለውን እንደጥሩ አጋጣሚ አድርጎ ነው

የሚመለከተው። ስለዚህም ይመስለኛል የከሸፈውና ገና ያልተፈታው የግንቦት 1997ቱ ሕዛባዊ ድል የስምምነቱ ሰነድ አካልም፤ የደራሲዎቹ ጥያቄም ያልሆነው። ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ የድሉ ባለቤት ነን ከሚሉ ድርጅቶችና ወገኖች (ስምምነቱን ከፈረሙት፤ አጋንነው ከተቀበሉትና ከጻፉለት) በኩል አንድም ኮስተር ያለ ጥያቄ አለመነሳቱ ነው። የሰኔውና የህዳሩ 1997 በወያኔ ጥይት የፈሰሰ የንጹህ ህዝብ ደም ምን ይለን ይሆን? ስንጠየቅስ የምንሰጠው መልስ? በወያኔ እስር ቤት ያሉትስ?

6. <u>ስብስቡ ከብሔርተኛ ሃይሎች መዳፍ በምንም መንገድ ሊወጣ የማይችልበት ገጽታው (Statue አንቀጽ 5፤ ገጽ 6)፡</u> በምርጫ ይሁን በስያሜ አይታወቅም ወይም ደግሞ ብዙውን ሥራ አስቀድሞ ስለሠራላቸው ወይም ስላየለባቸው የራስን አቅም የሚያዳቅቅ ካሳ ለመስጠት፤ ምንም ይሁን ምን፤ ኦነግ የፕሬዚዳንትነቱን ቦታ ይዟል። በዚህም ገጽታው ኦነግ ያለማጋነን ህወሀት በኢሕአዴግ ሰብስብ ውስጥ ለራሱ የሰጠውን ሚናም ተቀናጅቷል። በዚህም አንቀጽ መሠረት ሰብሳቢውም ሆነ ም/ሰብሳቢው ከያንዳንዱ ድርጅት ሦስት ተወካዮች የተወከሉበት ካውንስል (Governing Council: Article 4) በድምጽ ብልጫ ተመርጦ ለአንድ ዓመት ይሆናል ይላል። ጠበብ ያለ አጀንዳ ካላቸውና ኦነግን እንደ መሪያቸው አድርገው ሊያዩ ከሚችሉ የብሔር ስብስቦች ውስጥ አብላጫ አቅም ያለው ኦነግ እያለ፤ ቅንጅትም ሆነ፤ ይህንን ችግር አነጣጥሮ በማየት አስቀድሞ ወጣ እንጂ፤ ሕብረት፤ የመሪነቱን ቦታ ሊይዙ አይችሉም።

7. ስብስቡ ሲታሰብም ሆነ አስቀድሞ በወረቀት ተመሥርቶ በፊርማ ከጸደቀም በሁዋላ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ የጎላ ሚና ያላቸውንና ከሕዝቡ ጎን በመቆም ማናቸውንም መስዋዕትነት ሲከፍሉ የቆዩትንና አሁንም እየከፈሉ ያሉትን የሲቪክ ማህበራት (<u>ለምሣሌ፡</u> ኢመማ፤ ኢነጋማ፤ ኢሠመጉ) ና ያገር ሽማግሌዎችን ለመጨመር ደራሲዎቹ/አቀንቃኞቹ ፍላጎት አለማሳየታቸው ደግሞ ራሱን የቻለና የተወሳሰበ ችግር አለው። ምናልባትም እነዚህ ወገኖች የተተዉት የ"ነፍጠኛ" ስብስብ ተብለው ይሆን? አይደረግም አይባልም - የዚህ ዓይነቱን መሠረተ-ቢስ ክስ ከዚህ በፊት ሰምተናል ከአንድ የሲቪክ ማህበረሰብ መሪ የፖለቲካ ሥራ ጉብኝት ጋር በተያያዘ አጋጣሚ።

ከላይ በ 7-ነጥቦች የADF ሰነዶች ግምገማዬ ለማሳየት እንደሞከርኩት በኦነግ ስም የተበተነው ጽሁፍ የኦነግ እንጂ የሌላ ወገን ላለመሆኑ ተጨማሪ መደገፊያ መስጠቴ ነው። ጸሁፌን ከመደምደሜ በፊት ቀደም አድርጌ ገጽ 4 ላይ ያነሳሁዋቸውንና እንደገናም ከዚህ በታች ያሳየሁዋቸውን ጥያቄዎች፤ ይህንን ጽሁፍ ከጀመርኩ በሁዋላ ከወጣው የኦነግ ማስተባበያ ጋር አያይዤ ምላሽ እሰጥባቸዋለሁ። ጥያቄዎቹ፡

1) በኦነግ ስም እስከተጻፈስ ድረስ ኦነግ ላለመሆኑ፤ የአቶ ዳውድ ኢብሳን “የአደጋ መከላከያ/መቀነሻ” የራዲዮ ማስተባበያ ወደጎን ትተን፤ ልናቀርብ የምንችለው ሌላ የመከራከሪያ ሃሳብ ምን ሊሆን ይችላል? ለምንስ አስፈለገ?
2) ኦነግ ከሆነስ የኦሮሚፋ ቋንቋ እያለ እንዴት በአማርኛ ተጻፈ?
3) እንዴትስ አድርጎ ከአባላቱ እጅ አፈተለከ? የሠርጎ-ገብ ሤራስ ይሆን?

የመጀመሪያውን ጥያቄ በተመለከተ ቀደም አድርጌ ዝርዝር ማብራሪያ የሰጠሁበት ስለሆነ አልመለስበትም። ግና የወቅቱ የAFD ሰብሳቢና የኦነግ መሪ አቶ ዳውድ ኢብሳ ሰጡት በተባለዉ የራዲዮ መግለጫና አከታትሎም በድረ-ገጾች ወያኔን ተጠያቂ አድርጎ ጁን 9፣ 2006 የወጣው አርማ የሌለው የድርጅታቸው ጋዜጣዊ መግለጫና በእኔም አመለካከት "የ.........፣መልሶ ልብ ያደርቅ" ዓይነት ማስተባበያ ላይ አንዳንድ ሃሳቦችን መሠንዘር እፈልጋለሁ። በሁለቱም አጋጣሚዎች የተሰጠው መልዕክት ተመሣሣይ ስለሆነ ይህንን "A desperate minority regime continues with its malicious acts" በሚል ርዕስ በኢትዮ-ሚዲያ ድረ-ገጽ የወጣውን ጸሁፍ ዋና ዋና መከራከሪያ ሃሳቦች ብቻ እያነሳሁ ለመተቸት እሞክራለሁ።

<u>ጋዜጣዊ መግለጫው፡የወያኔን ተሪካዊና ወቅታዊ ሤራ አስመልክቶና ለዚህም ጽሁፍ ደራሲነቱ ጥርጣሬ በሌለው መልኩ ወያኔን ተጠያቂ ሲያደርገው የሚሰጣቸው ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ፦</u> (ከእንግሊዝኛ የተተረጎመ)

1) በትብብሩ (ADF) መመሥረት የተነሳ የብቸኛ አገዛዝ ዘመኑ እንደሚያጥር ስለተረዳ፣
2) ከዚህ በፊትም ቢሆን በተደጋጋሚ አጋጣሚዎች ተንቀሣቃሽ ስዕሎችን (ቪዲዮ) ጭምር በመፈበረክ የራሱ ሠራዊት የፈጸማቸውን ግፎች በኦነግ ላይ አላክኮ እንደነበር፣
3) ተቃዋሚው እንዳይደራጅና እንዳይፈታተነው፣ እንዲሁም አንድ እንዳይሆን በቅርቡ የስደተኛ ጉዳይ (Diaspora Affairs) በሚል መጠሪያ የሚሠራ ስብስብ በደጋፊዎቹ ዙሪያ እንደፈጠረና፣
4) "ኢትዮጵያ በ 2009 ዓ/ም" በሚል ርዕስ የኦሮሚያን ክልል አስፍቶ የሚያሳይ ካርታ አዘጋጅቶ ኦነግን ለመጉዳት በማሰራጨት ላይ እንዳለ የሚሉ ናቸው። ቀሪውን የፖለቲካ ሬቶሪክ የሚባለው ዓይነት መልዕክት ስላለው እንዳለ ትቸዋለሁ።

ስለዚህም እነዚህን እንመርምር። በርግጥ እንደተባለው፣ በተለይም ከተራ ቁ. 1-3 ያሉት የህወሀት/ኢሕአዴግን ባህሪ የሚገልጹ እውነታዎች ስለሆኑ የነዚህን ዕውነተኛነት ጥያቄ ውስጥ ማስገባት አይቻለኝም። የምጠይቀው ነገር ቢኖር የእነዚህ ዕውነተኛ መሆን እንዴት አድርጎ ወደ ኦነግ ድምዳሜ (የወያኔን ደራሲነት ለማረጋገጥ) ሊወስደን ይችላል ነው? በተራ ቁ. 4 የተመለከተው (በተለይ ደግሞ የካርታ ነገር ሲነሳ፣ ሁለቱም የሚጠየቁበት ጉዳይ ነው) የኦሮሚያን ካርታ በተመለከተ ወያኔ ኦነግን ለመነጠል ብሎ ሊያቀርብ እንደሚችል ባልጠራጠርም፣ ኦነግም ይህንን በተመለከተ የጸዳ አቋም የለውም፣ አብሬያችሁ ልሥራ ለሚላቸው ተቃዋሚዎችም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግልጽ ሆኖ መውጣት መቻል አለበት። ቀደም አድርጌ እንደገለጽኩት አሁንም ቢሆን በድረ-ገጹ የተጋነነና ታሪካዊ መሠረት የሌለውን ካርታውን ያሳያል። ካርታው በሰሜን እስከ አፋር ክልል፣ በደቡብ ሲዳማን ብቻ ሳይጨምር ሁሉንም ክ/ሃገሮች፣ በምዕራብ ከኢሉባቦር ቆርጦና ወለጋን እንዳለ ጨምሮ፣ በምሥራቅ ደግሞ "ኦጋዴንያ" ብሎ ከተወው የ "(ONLF) ክልል" በስተቀር እስከ ሐረር ዕንብርት ድረስ ያሳያል። ወያኔ ያደረገው ነገር ቢኖር፣ የርሱ ሥራ ከሆነ፣ ትልቁን ፎቶ ከኦነግ ተረክቦ የበለጠ አሳድጎ ማቅረብ ነው። እንግዲህ

ከኦነግ ማብራሪያ በቂ ምላሽ የተገኘ አይመስለኝም፤ ወደፊት የሚኖር ካለ እናያለን።

## ሁለተኛውን ጥያቄ (ኦሮሚፋ እያለለት እንዴት በአማርኛ ተጻፈ?) የሚለውን አመለካከት በተመለከተ፡

ይህንን ጥያቄ ሳስበው፤ በተለይም ደግሞ ካንድ ወገኔ ከሰማሁት በሁዋላ፤ መጠነኛ ጥርጣሬ ውስጥ ገብቼ ነበር። ይሁንና ደግሜ ደጋግሜ ሳስበውና ሳበራየው ግን አንድ ነገር ትዝ አለኝ - የኦሮምኛ ቋንቋ ገና አለማደጉ፤ ሁዋላ የተመረጠው ላቲንም እንዲሁ! በርካታው ኦሮሞ ወገኔም ደግሞ በአማርኛ እንደሚጽፍ፤ እነደሚያነብና እንደሚናገር! ኦነግ በግልጽ (ኦፊሻል) ደረጃ አማርኛን ቢኮንንም ተከታዮቼ የሚላቸው በርካታ ወገኖች ግን ከአማርኛ ሌላ (ቢያንስ በማንበብ ደረጃ) እንደማያውቁ ገባኝ። ስለዚህም በአማርኛ የመጻፍ አለመጻፉ ሁኔታ ዕንቅልፍ ሊያስነሳ የሚገባ ምክንያት አልመስል አለኝና ደራሲው ኦነግ ሊሆን አይችልም ወደሚለው ማፍረሻ አልወሰደኝም። ሌላም ምክንያት ማቅረብ ይቻላል - ጽሁፉ ድንገት በጠላት እጅ ከገባ እኛ አይደለንም ለማለት እንዲመች በአማርኛ ተጽፎስ ከሆነ? ሌላ ሦስተኛ ይሁንታ - በኦነግ ማስተባበያ በአማርኛ የመጻፉ ጉዳይ ራሱ እንደ ማጠየቂያ ተደርጎ አለመገለጹስ?

<u>ወደ ሦስተኛውና የመጨረሻው ጥያቄ እንሂድ፡ </u>(ጽሁፉ የኦነግ ከሆነ እንዴት አድርጎ ከአባላቱ እጅ አፈተለከ? የሠርጎ-ገብ ሤራስ ይሆን?

1. በእኔ ጽኑና ነገሮችን ሚዛን ውስጥ አስገብቶ ሊፈርድ ባዘነበለ የውስጥ ግምቴ (Intuition) ሊሆን የሚችለው ከእነዚህ ከሁለቱ ባንዱ ነው። ግና አንዱ ይሁን ሌላው ውጤቱ ከተጠያቂነት አኳያ ባመዛኙ ወደ አንድ አቅጣጫ ያመራል።

2. የመጀመሪያው ከሆነ፤ በኦነግ ውስጥ ባለው ወይም ሊኖር በሚችለው የአመለካከት ልዩነት ባንድ በኩል ጽንፈኛ የሆኑና ከኢትዮጵያዊ ሃይሎች ጋር መደራደር የማይፈልጉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያዊነታቸውን ሳይጠሉ ነገር ግን የፍትህ ጥያቄዎችን ጥያቄያቸው አድርገው በድርጅቱ ጥላ ስር የሚታገሉ፤ ነገር ግን የውስጥ ውይይቱ ያስፈራቸው ሃይሎች፤ ለተለያየ ዓላማም ቢሆን ይህንን ሰነድ ሊያጋልጡ ይችላሉ።

3. በሁለተኛው ከሆነ ደግሞ በኦነግ ውስጥ የወያኔ ወይም የሌላ የኦሮሞ ድርጅት ሠርጎ-ገብ አለ ማለት ነው፤ ከሠርጎ-ገብነት ተልዕኮው አኳያ ይህንን ሰነድ ግዴታ ማጋለጥ ይጠበቅበታል። በዚህ መልክ ከወጣም ሰነዱን የግዴታ የወያኔ ሥራ ሊያደርገው አይችልም።

4. ሦስተኛውን ይሁንታ (ከመጀመሪያው አንደኛ ይሁንታ አድርጌ የተመለከትኩት - የወያኔ ሚናን ማለት ነው) እነደገና እንመለስበት ብል የቀረ ነገር አጣሁ፤ ግን ወደፊት ለሚገኝ መረጃ ብንተወው ደህና ይመስለኛል። የህወሀት/ኢሕአዴግ ሆኖ

ቢገኝ ደስታውን አልችለውም። ለምን ቢባል ከኦነግም ሆነ ከሌሎች የብሔር ድርጅቶች ጋር የኢትዮጵያን ጉዳይ በጋራ መፍታት ግዴታ ነው ብዬ ስለማምን!

ጽሁፌን ከመደምደሜ በፊት ባንድ በኩል ለኦነግና ለቅንጅት አዲሶቹ መሪዎች/ተከታዮች፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለኢዴሃህና ለሲቪክ ማህበረሰብ መሪዎች አንዳንድ ጥያቄዎችን ለማቅረብ እወዳለሁ። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ፤ ያንዱ ከሌላው ቢከፋና ቢከረፋም፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግን ግልጽ ማድረግ ካለባቸው ጥያቄዎች አኳያ አንዳንድ የሚወራረሱ ባህርያት አሏቸው። የሁዋለኞቹ ደግሞ ኢትዮጵያን ከማዳን አንጻር ከፊተኞቹ ጋር እንዴት መሥራት እንደሚቻል ግልጽ ባልሆናችሁበት ሥፍራ ራዕያችሁን ግልጽ እንድታደርጉና በጥቅል የአመለካከት የጥፋትና የመጣ ይግዛኝ ዓይነት የፖለቲካ ዓውሎ-ነፋስ የመገፋት ግድየለሽ አመለካከት (Mass Apathy) ሊገፋና መደገፍ የማይገባውንም አካል/ስብስብ ሊደግፍ ለሚችለው የስሜት ተከታይ ወገን የምታውቁትንና በማስረጃ የተደገፈ መራራውን ዕውነት ጊዜ ሳትወስዱ እየነገራችሁ አደጋውን ራሱ ህዝቡ እንዲከላከለው እንድታደርጉ ለማሳሰብ ነው።

<u>ለኦነግና ለቅንጅት አመራር፤</u>

1. ትብብሩን ስትፈጥሩ የነበራችሁና ሌሎች ኢትዮጵያዊ ሃይሎች ያላወቁት ቀዳሚ ስምምነት ነበራችሁ ወይስ ቅንጅትም እንደ ኢዴሃህ ችግሩን አስቀድሞ አውቆና ቢቻልም አጀንዳውን ለማስቀየር ወይም ተቃውሞውን ለማሰማት ነው ወደ ሆላንድ የተመመው? የኢትዮጵያ ጉዳይና ሌሎች አወዛጋቢ ችግሮች ከሰነዱ ሲነበበቡና ኢዴሃህ አምርሮ ሲቃወም የቅንጅት አዲሶቹ መሪዎችስ፤ አቋማችሁ ቀድሜ ያነሳሁት ከነበረ፤ በተራችሁ ምን አላችሁ? ለምንስ ወደሁዋላ ቀርታችሁ ፊርማችሁን አሠፈራችሁ? ከራሳችሁ ድርጅት ደጋፊዎችስ ጥያቄዎች ሲቀርቡላቸሁ ምን መልስ ሰጣችሁ?

2. የኦነግ ራዕይ ግልጽ ነው፤ የቅንጅትስ? ከዚህ ስብስብ ለማግኘት የሚፈለገውስ ምንድን ነው? ከኤርትራስ ጋር ያላችሁስ ግንኙነት?

3. ኦነግ ይህ አወዛጋቢ ጽሁፍ የእኔ አይደለም ብሎ አጥጋቢ ማስረጃ ካቀረበ ልቀበለው ፈቃደኛ ነኝ፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ጽሁፍ ያወጣሁት የውስጥ ድርጅታዊ አንድነቴን ለማስጠበቅና ወደ ስምምነቱ ሂደት የአባሎቼን ድጋፍ ለማግኘት ብዬ አንጂ ፖሊሲዬ ሆኖ አይደለም ብሎ መግለጫ ካወጣ አሁንም ልቀበለውና ላምነው ፈቃደኛ ነኝ። ግና ኦነግ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ነውን?

4. ሰነዶቹ ከተበተኑና ህዘቡም ጥያቄ እያበዛ መምጣት ከጀመረ ወዲህ (በተለይም ደግሞ የእኔ አይደለም ብሎ ኦነግ የሚክደው ጽሁፍ ከወጣ ወዲህ) ቅንጅት ምን ያገኛል በሚል ምክንያት ነው አዲሶቹ ተመራጮች በስብስቡ ውስጥ ያቆያችሁት?

5. ቀደም አድርጎ ሕብረቱ በኢትዮጵያ የደረሰውን ቀውስ አስመልክቶ ተደጋጋሚ ጥሪ አድርጎላችሁ ነበር፤ ቅንጅትና ኦነግ ምን ምላሽ ሰጣችሁ? በዝምታችሁ ወያኔ ተጠቀመ ወይስ ተጎዳ?

## ለኢዴሃህና ለሲቪክ ማህበራት መሪዎች፡

1. ወያኔን/ኢሕአዴግን አስገድዶ ከሥልጣን ለማውረድም ሆነ የግንቦት 1997ቱን ሕዝበ-ውሳኔ እንዲያከብር ለማድረግ ካሉት ስብስቦች የሰፋ ስብስብ እንደሚያሻ ግልጽ ነው። በዚህ ረገድ ይህን ገና ካነሳሱ ችግር ያለበትን ትብብር ለውጦ ወይም ባዲስ ራዕይ "አድሶ" ለመጓዝ ጥረቱ መቀጠል ይኖርበታል። እስካሁን ለህዝብ ያልተጋለጡ ችግሮችም ካሉ ትንሽ በትንሽ ማውጣት መቻል አለባችሁ። ሲቪክ ማሕበራትም ብትሆኑ የህልውና ጉዳይ ነውና የኢትዮጵያ ፖለቲካ አያገባንም የምትሉ አይመስለኝም፤ ካላችሁም መሠረታዊ ስህተት ቁጥር አንድ ሊባል ይችላል። ሥልጣን መመኘትና ወደ ሥልጣን መገስገስ በቀዳሚነት የፖለቲካ ድርጅቶች አጀንዳ ቢሆንም፤ ሲቪክ ማሕበራትም በፖለቲካው ውስጥ ሚና አላቸው፤ ሊኖራቸውም ይገባል። ሕዝባዊነትና ፍትሃዊነት ያለውን ሥርዓት መመሥረት የሚቻለው በፖለቲካ ድርጅቶች ጫንቃ ብቻ ሊሆንም አይችልም፤ መሆንም የለበትም፤ የህልውናችሁም ጥያቄ ስለሆነ እናንተንም ይመለከታል።

2. ከደጋፊዎችም ሆነ ከተቃዋሚዎች የሚሠነዘሩ አስተያየቶችን በጥሞና መርምሮ፤ አስፈላጊም ሲሆን በገንቢ መልኩ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ሕዝብን ማስተማር ከእናንተ ይጠበቃል። ከሲቪክ ማህበረሰብም ጋር የሚደረገው ቅርርብ መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጣ በሚችልና ዘላቂነት ባለው መንገድ መከናወን ይኖርበታል። መብታቸውን ለማስከበር በየመግለጫዎቻችሁ የምታወጧቸው አቋሞቻችሁ ተስፋ የሚሰጡ ናቸው፤ በዚህም ግፋበት።

3. ይህ ቀጥዬ የምለው የሕብረቱ ችግር ባይሆንም በኢትዮጵያችን ውስጥ፤ ወደድንም ጠላን፡ በወያኔም ተገፍቶ፤ ካለፈ ታሪክም ተቀስቅሶ፤ አብዛኛውም ችግር በጎሣ ትምህርት ቤት ተፈብርኮ፤ አንዳንድ ጎሣዎችን ዓይን ለዓይን እንዳይተያዩ ያደረገና ያፈጠጠ ችግር ነው። ይህንን ችግር ባግባቡ ለማስተናገድ/ለመፍታት ያለንን ራዕይ፤ ዕቅድና ቁርጠኝነት ማስተማርና በተግባርም ማሳየት ይኖርብናል። ለዚህም አንዱ ዘዴ በወያኔም ይሁን በሌሎች ጽንፈኞች የሚገፉና ከፋፋይ የሆኑ የፖለቲካ ሤራዎችን አጥብቆ ማውገዝና ግንባር ሳያጥፉም መዋጋት ነው። ሌላው ደግሞ በስብስቡ የሚታቀፉትን ወገኖች ከሌሎች ባዕድ የሆኑና የኢትዮጵያን ጥፋት ከሚፈልጉ ሃይሎች ዕቅፍ ማውጣት ነው። ሁላችንም በዚህ መልክ ከተጓዝን ወዳሰብንበት ብሩህ ዓለም መድረሳችን አይቀርም።

| |
|---|
| በጽሁፌ ዋነኛ መልዕክት የሚሰማኝን ሁሉ ሳልደብቅና የ"መላላጥ" (የAppeasement) ቋንቋም ሳልጠቀም ማለት የሚገባኝን ሁሉ በግልጽ ብያለሁ። ይህን ያደረግኩት የእናት አገሬ፤ የ70 ሚልዮን ምስኪን ወገኖቼና የራሴም የህልውና ጥያቄ ስለሆነ ማንም ወገን ከሕዝብ ጀርባ ተመሣጥሮ እንዳፈተተው የአገሬን የወደፊት ዕጣ መወሰን አይችልምም፤ የለበትምም የሚል ጽኑ ዕምነትም ስላለኝ ነው።<br>ከተሣሣትኩ ግን ምን ጊዜም ለመታረም ዝግጁ ነኝ። ዘ.በ.<br>June 20, 2006 |

Zewdu Bekele is a member of the Center for Democracy and Social Justice of Ethiopia (CDSJE)